=====================>የጴንጤቆስጤ እውነት <==============================

ባለፈው ጊዜ ስለ ልሳን አስነብብያችሁ ነበር። ዛሬ ደግሞ ስለ ጴንጤቆስጤና በዛ ላይ ስለተደረጉት ድርጊቶች ከ#መጽሐፍ_ቅዱስ አብረን እንመለከታለን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ የእስራኤላዊያን ሰዎች ወደ እየሩሳሌም ሄደው የሚያከብሩት 3 ታላላቅ በዓላት አሉ። እነሱም ፋሲካ፣ ጴንጤቆስጤና የዳስ በዓል(Feast of Tabernacles) ይባላሉ። የጴንጤቆስጤ በዓል በአዲስ ኪዳን ብቻ ሳይሆን በብሉይ ኪዳንም የነበረ በዓል ነው። ዘሌ 23፡1-15። በዚህ በዓል ላይ የተደረጉ ነገሮች በምድር ብቻ የተወሰነ አይደለም። በሰማይም ሊካሔድ የነበረበት ሰርዓት አለ። ይህንን ለማብራራት ትንሽ ከርዕሳችን ወጣ ብዬ ስለ ክርስቶስ ልናገር። ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጐ ከተነሳ በኋላ ለ40 ቀናት ከደቀመዛሙርቱ ጋር ነበር። በዚህ ጊዜ በሰማይ ያለው ቤተመቅደስ ውስጥ የነበረውን ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን አብረን እንመልከት። በራዕይ ምዕራፍ 4 ላይ የእግዚአብሔር ቃል የሚናገር ነገር አለ። የዚህ ክፍል ዋና ሃሳብ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠ ነበረ። በዙሪያውም 24ቱ ሽማግሌዎችና 7 መብራቶች ይበሩ ነበር። እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚገባን ነገር ቢኖር 7ቱ የሚበሩት መቅረዞች የሚገኙት በቅዱሱ ክፍል ነው። ስለዚህ ይህ ክስተት የተከናወነው በቅዱሱ ክፍል ነው። ከዚህም በተጨማሪ 4ቱ ሐያዋን ፍጡራን ነበሩ። ቁጥር 11 ላይ “ጌታችንና አምላካችን ሆይ፤ ክብና ሞገስ፣ ሃይልም ልትቀበል ይገበሃል፤ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና፤ በፍቃድህም ተፈጥረዋልና ፤ ሆነዋልና።” ይህ ጥቅስ የሚሰጠን መልዕክት በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው ፈጣሪ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጥሯልና። በዚህ ክፍል ላይ ክርስቶስ ተገልጾ አንመለከትም መላዕክቶችም ተገልጸው አንመለከትም። ወደ ምዕራፍ 5 ቁጥር 6 ስንሔድ አንድ ነገር እንመለከታለን። ክርስቶስ ወደ በመላዕክት ታጅቦ ሰማይ እንደሔደ። ቁጥር 6 እንዲህ ይላል “ከዚያም በዙፋኑና በአራቱ ሕያዋን ፍጡራን፣ በሽማግሌዎቹ መካከል #የታረደ_የሚመስል_በግ_ቆሞ አየሁ…” በዚህ ምዕራፍ 5 ላይ ክርስቶስ በቤተመቅደሱ ቅድሱ ክፍል ላይ ሆኖ እናያለን። በዚህ ጊዜም 24ቱ ሽማግሌዎች መዝሙራቸውን መዘመር ቀጠሉ። ይህንን ምዕራፍ ሙሉን እንድታነቡ አደፋፍራችኋለው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እግዚአብሔር ደስ የተሰኘበትን መሰዋዕት እሳትን ከሰማይ በመላክ መሰዋዕቱን እንዲበላ ያደርግ ነበር። ለምሳሌ የኤልያስን ታሪክ ማየት እችላለን ሌሎች ሌሎችም። ክርስቶስ ለተፈጠሩት ሰዎች በሙሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ህይወቱን መሰዋዕት አድርጐ አቀረበ። እግዚአብሔርም ይሄንን መሰዋዕት ተቀበለ። ከዛም እሳት የሚመስል ልሳኖችን በደቀመዛሙርቱ ላይ በማድረግ የምስራቹ ወንጌል ለአለም ሁሉ እንዲሰራጭ ሆነ። ምን አይነት የሚያስደነቅ አምላክ ነው ያለን? እዚህ ላይ አንድ ነገር መጨመር የምፈልገው ነገር ቢኖር ደቀመዛሙርቱ 11 ሆነው እያለ (ከሃዲው ይሁዳ ስለሞተ) 1 ሰው መጨመር አስፈላጊ ነበር። ምክንያቱም ክርስቶስ የቤተመቅደሱን አገልግሎት ሲጀምር ካህናት የሚያደርጉት ልብስ ውስጥ የደረት ኪስ የሚባለው 12 ቦታዎች (buttons) ነበሩት። ይሄንን ለማሟላት ደቀመዛሙርቱ ልክ ክርስቶስ እንደመረጠ 12 መሆን ስለነበረባቸው ማቲያስ ተመረጠ። ሐዋ 1፡25-26።

ይህ ጽሁፍ ርዕሱን ለማብራራት ብዙ በጥልቀት መየት የሚገባንን ትምህርት በጨረፍታ ተመልክተነዋል። ነገር ግን ጥያቄ እና ሃሳብ ካላችሁ ሁሌም በሮቼ ክፍት ሆነው ይጠብቋችኋል። የእግዚአብሔር ፀጋ ይብዛላችሁ። እወዳችኋለው። ተባረኩ።